በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ፍትሕ ቢሮ
የሕግ ምክር፣ማ ርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር፡- የሕ/ምክ/ማር/ማጠ/4036/18

ቀን 28/04/2018 ዓ/ም

**ለአብክመ ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን**

<u>ባህርዳር</u>

**ጉዳዩ፡- <u>የመመሪያ ምዝገባን ይመለከታል</u>**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአስተዳደር ሥነ ሥርዓትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 292/2017 አንቀጽ 16(4) መሰረት ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በስራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አስመልክቶ አዋጁ በወጣ በአንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮ በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

ተቋማችሁ በአዋጁ መሰረት በቁጥር ት/ሎ/ባ/03/-360/18 በቀን 24/03/18 ዓ/ም በተፃፈ ሸኚ ደብዳቤ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 18/2016ን የላካችሁልን መሆኑ ይታወቃል፡፡

በእኛም በኩል የተላከልንን ይህን መመሪያ በአዋጁ መሰረት ተመልክተን መመሪያ ቁጥር 18/2016 ተብሎ ይጠራ የነበረውን በመመዝገብ በአዲስ **መመሪያ ቁጥር 33/2018 ዓ/ም** በሚል ሰጥተን የላክንላችሁ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

መስፍን መኮንን

የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት
የክልል ዐቃቤ ሕግ

<u>ግልባጭ</u>

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤(ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት

<u>ፍትህ ቢሮ</u>

# መመሪያ ቁጥር 33/2018 ዓ/ም

# በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ማሻሻያ መመሪያ

ለትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን የክልሉን የትራንስፖርት መሰረተ ልማት በማስፋፋት፤ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር፤ አገልግሎት አሰጣጡን በቴክኖሎጅ በማስደገፍ፤ ህግና ስርአትን በማስከበር፤ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፤ ምቾቱና ደህንነቱ የተጠበቀ የትራንስፖርትና የሎጀስቲክስ አገልግሎት እንዲሰጥ ተልዕኮ የተሰጠው በመሆኑ፤

ተቋሙ የሚሰጣቸውን የአገልግሎት አይነቶች፣ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚያስከፍለውን ክፍያ እና ከአገልግሎቱ የተሰበሰበዉ ገንዘብ ለምን ለምን አገልግሎት መዋል እንዳለበት ግልፅ የሆነ እና በመመሪያ የተደገፈ አሰራር ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በመደበኛ በጀት እጥረት ምክንያት የአገልግሎት መስጫ ግብዓቶችን በአግባቡ ባለመሟላታቸው ፈጣን አገልግሎት ማግኘት ያልቻሉ ደንበኞች ጥያቄ አግባብ ባለው መልኩ ምላሽ መስጠት በማስፈለጉ፤

በየስራ ክፍሉ የተዘጋጁ የታሪፍ እና የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም መመሪያ ወጥ የሆነ መመሪያ ማዘጋጀት በማስፈለጉ፤

የተገልጋዩን ህዝብ ፍላጎት ያረካ ቀልጣፋ እና ዘመናዊ አገልግሎትን መፍጠሩ፣ ትራንስፖርት ዘርፉ ከመንገድ ቢሮ ተገንጥሎ እራሱን ችሎ መደራጀቱ፣ የሎጀስቲክስ አገልግሎቱ ከትራንስፖርት ዘርፉ ጋር ተቀላቅሎ እንዲሰጥ በክልሉ ምክር ቤት መወሰኑ፣ ያለ ክፍያ ሲሰጡ የነበሩ አገልግሎቶችን ክፍያ እንዲኖራቸው ማስቻሉ፣ ከወቅታዊ ሁኔታው ጋር የተገናዘበ የአገልግሎት ክፍያዎችን አጥንቶ ማሻሻል ማስፈለጉ፣ በውስጥ ገቢ በጀት መሸፈን ያለባቸው ተጨማሪ የወጭ አርዕስቶችን ማካተቱ እንደ ምክንያት መምሪያ ቁጥር 015/2013 ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 199/2014 አንቀፅ 7 ንኡስ አንጽ 42 እና አንቀጽ 18 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን የተሻሻለ መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1.አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 33/2018 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2.ትርጓሜ

በደንቡ ትርጓሜ የተሰጣቸው ቃላት እንደ አግባቡ በዚህ መመሪያ ተፈጻሚ መሆናቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የማይሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፡-

1/ **"ደንብ"** ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን ማቋቋሚያ በደንብ ቁጥር 199/2014 ነው፤

2/ **"ባለስልጣን"** ማለት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ነው፤

3/ **"ክልል"** ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ማለት ነው፤

4/ **"ጽህፈት ቤት"** ማለት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ስር የሚገኙ የሪጅኦፖሊታን ከተሞች፣ የዞን እና የብሄረሰብ ዞን የትራንስፖርት ጽ/ቤቶችን ማለት ነው፤

5/ **"ቡድን"** ማለት በዞን ትራንስፖርት ጽ/ቤቶች፣ በሜትሮ ፖሊታንት እና በሪጅኦፖሊታን ከተማ ትራንስፖርት ተጠሪ ጽህፈት ቤቶች ስር የሚገኙ አገልገሎት የሚሰጡ የስራ ቡድኖችን የሚገልፅ ነው፤

6/ **"የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ"** ማለት ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን ለማሽከርከር የሚያስችል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በወጣው

የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 መሠረት የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

7/ **"ከአገልግሎት የሚገኝ ገቢ"** ማለት በትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ባለስልጣን ስር በተደራጁ ዳሬክቶሬቶች እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ስር ባሉ የዞን እና በሪጅኦፖሊታንት ከተማ ትራንስፖርት ጽ/ቤቶች ስር ያሉት በአሽከርካሪ፣ በተሽከርካሪ፣ በትራንስፖርት ልማት፣ በትራንስፖርት ስምሪት፣ በመንገድ ደህንነት፣ እና በትራንስፖርት አገልግሎት ኢንስፔክሽን ብቃት ማረጋገጫ ቡድኖች ከሚሰጡት አገልግሎቶች የሚሰበሰብ የውስጥ ገቢ ነው፤

8/ **"የትራንስፖርት አገልግሎት ልማት፤የትራንስፖርት አገልግሎት ኢንስፔክሽን፤ የመንገድ ደህንነት፣ የትራንስፖርት ስምሪት፣ የአሽከርካሪ እና የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ በጀት"** ማለት በባለስልጣኑ እና የተዋረድ ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥን ለማሳለጥ የሚያስችሉ ግብዓቶችን ለማሟላት፣ የትራፊክ ኮምፕሌክስን በአግባቡ ለማደራጀት፣ በስራ ላይ የሚያጋጥሙ ብልሽቶችን በወቅቱ አስጠግኖ ያልተቆራረጠ አገልግሎት ለመስጠት፣ የአገልግሎት አሰጣጡን ሊያዘምኑ የሚችሉ ልዩ ልዩ ቴክኖሎጅዎችን እና አሰራሮችን ለማልማት እና ለሌሎች ለዚሁ ስራ አገልግሎት ማሚያ የሚውል የዉስጥ ገቢ በጀት ማለት ነው፤

9/ **"የኢንስፔክሽን የቴክኒክ ቅጣት ገንዘብ ማለት"** ማንኛውም ባለሞተር ተሽከርካሪ አገልግሎት ሲሰጥ ቴክኒካል አቋሙ ተሟልቶ ሳይገኝ ጉዳዩ በሚመለከታቸው የቴክኒክ ባለሙያዎች በሚሰጥ የሙያ አስተያዬት መሰረት የሚወሰን ቅጣት ነው፤

10/ **"የጥገና ወጭ"** ማለት ከአሽከርካሪ እና ከተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን አገልግሎቶች ለመስጠት የመንጃ ፈቃድ ሲስተም ሶፍትዌር ብልሽት፣ የትራፊክ ኮምፕሌክስ ብልሽት፣ የትራፊክ ኮምፕሌክስ ህንፃዎች፣ የመንጃ ፈቃድ ማተሚያ ማሽን፣ ኮምፒውተር፣ ራዳር እና የመሳሰሉትን ጥገና ለማስጠገን የሚውል ወጭ ነው፤

11/ **"የአገልግሎት ክፍያ"** ማለት ተቋሙ ለሚሰጣቸዉ የተለያዩ አገልግሎቶች የሚያስከፍላቸዉ ክፍያ ማለት ነዉ፤

12/ **"የኮምፒዩተር ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ"** ማለት ማንኛዉም የአሽከርካሪ እና የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት፣ ለማሳደስ፣ የእድሳት ጊዜያቸው ላለፈባቸው በቅጣት

የሚሰበሰብ ክፍያ፣ ቅጅ ወይም የትክ አገልግሎት ሲሰጥ ለሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ነዉ፤

13/ **"የሞተር ለውጥ"** ማለት አንድ ተሽከርካሪ በተለያየ ምክንያት ከሞተሩ ላይ ችግር ሲያጋጥመውና መስተካከል የማይችል ሲሆን ከቀድሞው ሞተር ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሞተር በመተካት የሚደረግ የሞተር ለውጥ ማለት ነው፤

14/ **"የሻንሲ ለውጥ ማድረግ"** ማለት አንድ ተሽከርካሪ በተለያየ ምክንያት ከሻንሲ ላይ ችግር ሲያጋጥመውና መስተካከል የማይችል ሲሆን ከቀድሞው ሻንሲ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሻንሲ በመተካት የሚደረግ የሻንሲ ለውጥ ማለት ነው፤

15/ **"ያለ ፈቃድ የሞተር የሻንሲ የአካል ለውጥ ማድረግ"** ማለት ፋይሉ ያለበት ትራንስፖርት ጽህፈት ቤት መመሪያውን ተከትሎ እንዲቀይር ስምምነት ሳይሰጥ መቀየር ማለት ነው፤

16/ **"የምርመራ ሰርተፊኬት"** ማለት ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ አድርጎ የቴክኒክ ብቃቱን ላሟላ ተሽከርካሪ የሚሰጥ ምርመራ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ነው፤

17/ **"የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራ"** ማለት የተሽከርካሪ ምርመራ ተሽከርካሪው አደጋን በማያስከትል ሁኔታ በመንገድ ላይ መሽከርከር ስለመቻሉ በእይታ በቴክኒሽያኖች አማካኝነት የሚካሄድ ምርመራ ማለት ነው፤

18/ **"ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት /ቦሎ/"** ማለት አንድ ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ ለመንቀሳቀስ የቴክኒክ ብቃትና ምቾት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚሰጥና ለአንደ ዓመት የሚፀና ተለጣፊ ምልክት ነው፤

19/ **"የተሽከርካሪ ምርመራ"** ማለት አንድ ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ የቴክኒክ ብቃትና ምቾት ያለው መሆኑንና መንቀሳቀስ የመቻል ብቃቱን ለማረጋገጥ የሚደረግ የቴክኒክ ምርመራ ነው፤

20/ **"ቀረጥ"** ማለት በትክክል ለእቃው በተደረገ ጠቅላላ ወጭ ላይ ተመስርቶ እና የዓለም አቀፍ የተዋሃደ የሸቀጦች አሰያየምና አመዳደብ ሥርዓትን ተከትሎ በወጣው የጉምሩክ የታሪፍ ደንብ መሠረት በገቢና ወጪ እቃዎች ላይ የሚጣልና የሚሰበሰብ ታሪፍ ነው፤

21/ **"የቴምብር ቀረጥ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 110/1990 መሠረት ማንኛውም ሰው ንብረት በስሙ ሲያስመዘግብ በስሙ በሚያስመዘግበው የንብረት መጠን ተሰልቶ የንብረቱን መጠን 2% ለመንግስት እንዲከፍል ማድረግ ማለት ነው፤

22/ **"ሞተር ብስክሌት"** ማለት በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ እና ባለሦስት እግር /wheel/ ሆኖ ሰው ብቻ ለማጓጓዝ የሚያገለግል ነው፤

23/ **"ትራይ ሳይክል/ባለ ሶስት እግር /ባጃጅ/"** ማለት በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ እና ባለሦስት እግር /wheel/ ሆኖ ሰው ወይም ዕቃን ለማጓጓዝ የሚያገለግል ነው፤

24/ **"ልዩ ተንቀሳቃሽ"** ማለት ሰው ወይም ዕቃን በመንገድ ላይ እንዲያመላልስ ሆኖ የተሰራ ተንቀሳቃሽ ሳይሆን ለእርሻ፤ ለአትክልት፣ ለከብት፣ ለመንገድ፣ ለህንፃ፣ ለቁፋሮ ወይም ለማንኛውም ተመሳሳይ ስራ የተሰራ ወይም ለዚህ ጉዳይ እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

25/ **"ስም ማዛወር"** ማለት በሽያጭ፣ በስጦታ፣ በውርስና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በመሳሰሉት ምክንያቶች በተሽከርካሪ ላይ የሚከናወን የባለቤትነት ይዞታ ለውጥን የሚያጠቃልል ነው፤

26/ **"የምዝገባ አገልግሎት ለውጥ"** ማለት ተሽከርካሪው ከሚሰጠው አገልግሎት ወደ ሌላ አገልግሎት ዘርፍ ሲቀየርና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሠሌዳ ኮድ በመለወጥ የሚከናወን ነው፤

27/ **"የምዝገባ ስረዛ"** ማለት አንድ ተሽከርካሪ ተመዝግቦ ሲሰራበት ከነበረው አገልግሎት በእርጅና፣ በአደጋ፣ በመለዋወጫ/spare parts/ ዕጥረት ተሽከርካሪው ከአገልግሎት ውጭ በመሆኑ ሠሌዳና ሊብሬ ሲመልስ የሚከናወን ስረዛ ማለት ነው፤

28/ **"አዲስ ተሽከርካሪ ምዝገባ"** ማለት ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ወይም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን ምዝገባ ያልተደረገላቸው አዲስም ሆነ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎችን አዲስ ምዝገባ የተደረገለት ተሽከርካሪ ማለት ነው፤

29/ **"ቋሚ ሰሌዳ"** ማለት አንድ ተሽከርካሪ የሚያስፈልጉት ህጋዊ ሰነዶች ተሟልተውና ተገቢው ምርመራና ምዝገባ ከተደረገለት በኋላ ከተሽከርካሪው ከፊትና ከኋላ የሚለጠፍ በስራ /አገልግሎት/ ዓይነት ተለይቶ የሚሰጥ ቋሚ የሰሌዳ ቁጥር ነው፤

30/ **"ከቀረጥ ነፃ"** ማለት በጉምሩክ ደንብ መሠረት በገቢ.ና ወጭ እቃዎች ላይ ከሚጣልና ከሚሰበሰብ ቀረጥና ታክስ ነፃ መሆን ማለት ነው፤

31/ **"የሻንሲና የሞተር ቁጥር ምት ምዝገባ አገልግሎት"** ማለት አንድ ተሽከርካሪ በጉዳት እና በተለያየ ምክንያት የሞተር ቁጥር ወይም የሻንሲ ቁጥር በአዲስ ሲቀይር የቀድሞውን ቁጥር በመቀየር አዲሱን የመመዝገብ ተግባር ማለት ነው፤

32/ **"ሊብሬ"** ማለት የተሽከርካሪ መሠረታዊ ክፍሎች እና የባለንብረቱ ስም የተፃፈበት ተሽከርካሪው በህጋዊ መልኩ ምዝገባ ለማድረጉ እና ለባለንብረቱ የንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ በትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት የሚሰጥ ደብተር ነው፤

33/ **"አዲስ ተሽከርካሪ"** ማለት ወደ ሀገር ውስጥ ከመግባቱ በፊት በሌላ ሀገር ተመዝግቦ አገልግሎት ያልሰጠ ሆኖ ሁለት ዓመት ያልበለጠው ተሽከርካሪ ማለት ነው፤

34/ **"ያገለገለ ተሽከርካሪ"** ማለት ወደ ሀገር ውስጥ ከመግባቱ በፊት በሌላ ሀገር ተመዝግቦ አገልግሎት ሰጥቶ ወደ ሀገር የገባ ተሽከርካሪ ማለት ነው፤

35/ **"የስልጠና ምድብ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 1074/2010 ላይ የማሽከርከር ብቃት የስልጠና ምድቦችን (አውቶ፣ ባለሶስት እግር፣ ህዝብ 1፣ ህዝብ 2፣ ህዝብ 3፣ ደረቅ 1፣ ደረቅ 2፣ ደረቅ 3፣ ፈሳሽ 1 ፈሳሽ 2 እና የልዩ ማሽነሪዎች የማሽከርከር የብቃት ማረጋገጫ ያጠቃልላል።

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን እና በተዋረዱ በሚገኙ ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

# ክፍል ሁለት

## ስለ ውስጥ ገቢ ምንጮች

## ንዑስ ክፍል አንድ

## የውስጥ ገቢ ምንጮች

4. **የውስጥ ገቢ ምንጮች**

1/ ከአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ፡-

1) የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሰጥ (ለሁሉም ምድብ)፤

2) የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ተበላሽቶ ትክ ሲሰጥ (ለሁሉም ምድብ)፤

3) የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ጠፍቶ ትክ ሲሰጥ (ለሁሉም ምድብ)፤

4) አሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲታደስ (ለሁሉም ምድብ)፤

5) አሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እድሳት ጊዜው ሲያልፍ (ለሁሉም ምድብ) ቅጣት፤

6/ የእድሳት ጊዜው አንድ ዓመት ካለፈው የንድፈ ሃሳብ እና የተግባር ለመፈተን፤

7) የመንግስት ተሿሚዎች የማሽከርካር ልዩ መንጃ ፈቃድ ሲሰጥ፤

8) የመንግስት ተሿሚዎች የማሽከርካር ልዩ መንጃ ፈቃድ ሲታደስ፤

9) የመንግስት ተሿሚዎች የማሽከርካር ልዩ መንጃ ፈቃድ የማደሻ ጊዜው ሲያልፍ ቅጣት፤

10) መንጃ ፈቃድ ከመከላከያ ወደ ሲቪል ለመቀየር (ለሁሉም ምድቦች)፤

11) የመንጃ ፈቃድ ፋይል ዝውውር (ለሁሉም ምድቦች ለመላክም ሆነ ለመቀበል)፤

12) የቴክኒሻን (የአፕሮቫል) ብቃት ማረጋገጫ ማሰልጠኛ ተቋም ፈቃድ ሲሰጥ፤

13) የቴክኒሻን (የአፕሮቫል) ብቃት ማረጋገጫ ማሰልጠኛ ተቋም ፈቃድ ሲታደስ፤

14) የቴክኒሻን አዲስ ወይም ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ (የአፕሮቫል ሰርትፍኬት) ሲሰጥ (ለሁሉም ምድብ)፤

15) የተክኒሻን የብቃት ማረጋገጫ (አፕሮቫል ሰርትፍኬት) ለማደስ (ለሁሉም ምድብ)፤

16) የተከኒሻን የብቃት ማረጋገጫ የእድሳት ጊዜው ሲያልፍ (ለሁሉም ምድብ በአንድ ካርድ)፤

17) የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ወይም የራሳቸውን ሰራተኞች ለሚያሰለጥኑ ሌሎች ተቋማት አዲስ ወይም ምትክ ፈቃድ ሲሰጥ፤

18) የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ወይም የራሳቸውን ሰራተኞች ለሚያሰለጥኑ ሌሎች ተቋማት ፈቃዳቸው ሲታደስ፤

19) የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት የፈቃድ እድሳት ጊዜው ሲያልፍ ቅጣት፤

20) የልዩ ማሽነሪ ማሰልጠኛ ተቋም ፈቃድ ሲሰጥ፤

21) የልዩ ማሽነሪ ማሰልጠኛ ተቋም ፈቃድ ሲታደስ፤

22) ልዩ ማሽነሪ ማሰልጠኛ ተቋም ፈቃድ የማደሻ ጊዜው ሲያልፍ ቅጣት፤

23) የሀገር ውስጥ መንጃ ፈቃድ ስምምነት ላላቸው አገሮች ደብዳቤ ለመፃፍ፤

24) የውጭ ሀገር መንጃ ፈቃድ ለሚያመጡ ወደ ሀገር ውስጥ ለመቀየር፤

25) ለመደበኛ ሰልጣኞች የተግባር እና የንድፈ ሃሳብ ፈተና ቀጠሮ ማሳዣ፤

26) ፈተና ለወደቁ ዳግም የተግባር እና የንድፈ ሃሳብ ለመፈተን ቀጠሮ ማሳዣ፤

27) የማስፋፊያ ጥያቄ ለሚያቀርቡ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት የአገልግት ክፍያ፤

28) ቅርንጫፍ (ብራንች) ለመክፈት ጥያቄ ለሚያቀርቡ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት የአገልግሎት ክፍያ፤

29) ማሰልጠኛ ተቋማት ሰልጣኞቻቸውን ለፈተና ወደ ትራፊክ ኮምፐሌክስ ሲያስገቡ የዳግም ፈተና ጨምሮ ለአንድ ሰልጣኝ የኮቲ ክፍያ፤

30) በፈተናም ሆነ መልምመድ ወቅት በሰልጣኞች እና ወይም በአሰልጣኞች ምክያት በትራፊክ ኮምፐሌክሱ ላይ ማንኛውንም ዓይነት ጉዳት በሚያደርሱበት ጊዜ ከጉዳቱ አይነትና መጠን ጋር በተጣጠመ መንገድ በ3 ቀን ማስተካከል ወይም ማስቀየር ወይም ማሳደስ አለበት። ማሰልጠኛ ተቋሙ ይህን ማድረግ ካልቻለ በህግ አካል ክስ እንዲመሰረት ያደረጋል። በትራፊክ ኮምፐሌክስ ውስጥ የሚደርስን ደንብ መተላለፍ

ጨምሮ ወደፊት የትራፊክ ኮምፕሌክስ ዝርዝር የአስተዳደር መመሪያ ይዘጋጃል፡፡

2/ ከተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ፡-

1) ያለፈቃድ ተሽከርካሪውን የአካል ለውጥ ያደረገ ቅጣት፤
2) ያለፈቃድ በተሽከርካሪው ላይ የሞተር ለውጥ ያደረገ ቅጣት፤
3) ያለፈቃድ በተሽከርካሪው ላይ የሻንሲ ለውጥ ያደረገ ቅጣት፤
4) ያለፈቃድ በተሽከርካሪው ላይ የሞተር ቁጥር ያስመታ ቅጣት፤
5) ያለፈቃድ በተሽከርካሪው ላይ የሻንሲ ቁጥር ቅጣት ቅጣት፤
6) የተለያዩ ሰሌዳወች (ለተላላፊ፣ የእለት፣ መደበኛ/ቋሚ ሰሌዳዎች) ሲሰጥ፤
7) የተሽከርካሪ የባለቤትነት ማስመዝገቢያ የቴምብር ቀረጥ 2 ከመቶ ክፍያ፤
8) ዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ እና የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት ( ቦሎ) ሲሰጥ፤

(ሀ) ለሞተር ሳይክል፣

(ለ) ለግል አውቶሞቢሎች፣

(ሐ) የተለያየ ክብደት የመጫን አቅም ላላቸው የጭነት ተሽከርካሪዎች፣

(መ) ለልዩ ተንቀሳቃሽ መሳሪያዎች (ተሽከርካሪዎች)፡፡

9) ለዓመታዊ ምርመራ ተለጣፊ ምልክት (ቦሎ) ግልባጭ መስጠት፡-

(ሀ) የተለጣፊ ምልክት ስህተት፣

(ለ) የተለጣፊ ምልክት ብልሽት፣

(ሐ) የተለጣፊ ምልክት የእድሳት ጊዜው ሲያልፍ ቅጣት፡፡

10) የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ምርመራ ሲደረግ፤
11) የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ ሊብሬ ሲሰጥ፤
12) ሊብሬ ስህተት፣ ሲበላሽ፣ ወይንም ሲጠፋ ምትክ ሲሰጥ፤
13) የተሽከርካሪ የአካል ለውጥ ፈቃድ አገልግሎት ሲሰጥ፤
14) የተሽከርካሪ የአካል እና የአገልግሎት ለውጥ ምዝገባ አገልግሎት ሲሰጥ፤
15) የሻንሲ እና የሞተር ለውጥ ፈቃድ አገልግሎት ሲሰጥ፤
16) የሻንሲ ለውጥ ምዝገባ አገልግሎት ሲሰጥ፤
17) የሞተር ለውጥ ምዝገባ አገልግሎት ሲሰጥ፤
18) የሻንሲ ቁጥር እና የሞተር ቁጥር ማስመቻ ፈቃድ አገልግሎት ሲሰጥ፤
19) የተሽከርካሪ የእዳ እና እገዳ ምዝገባ አገልግሎት ሲሰጥ፤
20) የተሽከርካሪ የእዳ እና እገዳ ምዝገባ ስረዛ አገልግሎት ሲሰጥ፤

21) የነዳጅ አጠቃቀም ልኬታ ኖርማላይዜሽን ሲሰራ፤

22) የተሽርካሪ ሽያጭ ውል ማፍረስ፤

23) የተሽከርካሪ የባለቤትነት የስም ዝውውር አገልግሎት ሲደረግ፤

24) የተሽከርካሪ ፋይል ከአማራ ክልል ወደ ሌሎች ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ማዛወር፤

25) ከሌሎች ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ወደ አማራ ክልል የሚመጡ የተሽከርካሪ የፋይል ዝውውር አገልግሎት ሲካሄድ፤

26) ህግና ስርዓትን ለማስከበር ከፍርድ ቤት፣ ከፍትህና ከፖሊስ ተቋማት መረጃ ሲጠየቅ በነፃ የሚስተናገዱበትን በሲስተሙ ላይ የሚመቻች ሆኖ ሌሎች ህጋዊ ለሆኑ አካላት መረጃ ሲሰጥ፤

27) የተሽከርካሪ ሊብሬ እና ሰሌዳ በአደራ ማስቀመጥ አገልግሎት ሲሰጥ፤

28) ተመዝግቦ የነበር ተሽከርካሪን ለመሰረዝ የሚከፈል፤

29) ከገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን በሚፃፍ ደብዳቤ ከቀረጥ ነፃ ለገባ ተሽከርካሪ ቀረጥ ማንሳት አገልግሎት ሲሰጥ፤

30) ለጠፋ ቦሎ፣ ሊብሬ፣ ሰሌዳ እንዲሁም ሌሎች ማፈላለጊያ ለፖሊስ ወይም ለፕረስ ለሚሰጥ መረጃ፤

31) አዲስ የተሽከርካሪ አስመጭነት ፈቃድ መስጠት እና ማደስ፤

32) ያገለገለ የተሽከርካሪ አስመጭነት ፈቃድ መስጠት እና ማደስ፤

33) የፍጥነት መገደቢያ ፈቃድ መስጠትና ማደስ፤

34) ቴምብር ቁርጥ፡-

(ሀ) የሻንሲ ለዉጥ 2 መቶኛ ክፍያ፣

(ለ) የሞተር ለዉጥ 2 መቶኛ ክፍያ፣

(ሐ) የአካል ለዉጥ 2 መቶኛ ክፍያ፣

(መ) የተሽከርካሪ ጨረታ ሽያጭ 2 መቶኛ፣

(ሠ) አዲስ ተሽከርካሪ ለማስመዝገብ 2 መቶኛ ክፍያ፡፡

35) የተሽከርካሪ ዋጋ መገመቻ አገልግሎት፡-

(ሀ) ለሞተር ብስክሌት፣

(ለ) እስከ አምስት መቀመጫ አውቶሞቢልና ሦስት እግር ሞተር ሣይክል፣

(ሐ) ከ6-17 መቀመጫና ከ1-15 ኩንታል፣

(መ) ከ18-44 መቀመጫና ከ16-49 ኩንታል፣

(ሠ) ከ45 መቀመጫ በላይና ከ50-100 ኩንታል፣

(ረ) ከ100 ኩንታል በላይ፣

(ሰ) ለልዩ ተንቀሳቃሽ፡፡

36) የተለያዩ ደረጃ ላላቸው የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት የፈቃድ መስጫ ክፍያ፤ የፈቃድ ማደሻ ክፍያ እና ፈቃዱን በወቅቱ ላላሳደሱ የቅጣት ክፍያ፤

37) የተለያዩ ደረጃ ላላቸው የተሽከርካሪ ጥገና የፈቃድ መስጫ ክፍያ፣ የፈቃድ ማደሻ ክፍያ እና ፈቃዱን በወቅቱ ላላሳደሱ የቅጣት ክፍያ፤

38) የጀልባ ብቃት ፈቃድ ሲሰጥ ከሚከፈል፤

39) የጀልባ ብቃት ፈቃድ ሲታደስ ከሚከፈል፤

40) የጀልባ ብቃት ፈቃድ እድሳቱ ሲያልፍ የቅጣት ክፍያ፤

3/ ትራንስፖርት አገልግሎት ኢንስፔክሽን

ትራንስፖርት አገልግሎት ኢንስፔክሽንን ገቢን አስመልክቶ የሚሰበሰበው በመንገድ ላይ እና በመናኸሪያ የተሽከርካሪ ድንገተኛ ቴክኒክ ምርመራ በማካሄድ ከአገልግሎት እና ከቅጣት ገቢ ሆኖ በምርመራ ወቅት የሚገኙ የቴክኒክ ጉድለቶች ቀላል እና ከባድ በሚል ተከፍለው ቀላል ችግሮች እስከ 7 ቀን እና ከባድ ችግሮች ደግሞ እስከ 10 ቀን ባለው ተስተካክለው መቅረብ የሚገባቸው ሲሆን፣ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፦

1) የባለሁለት እና ሦስት እግር ተሽከርካሪ ምርመራ ሲካሄድ ከሚከፈል፤
2) እስከ 11 ሰው መቀመጫ ያላቸው ተሽከርካሪዎች ምርመራ ሲካሄድ ከሚከፈል፤
3) ከ12 እስከ 44 መቀመጫ ያላቸው ተሽከርካሪዎች ምርመራ ሲካሄድ ከሚከፈል፤
4) 45 ሰውና በላይ መቀመጫ ያላቸው ተሽከርካሪዎች ምርመራ ሲካሄድ የሚከፈል፤
5) እስከ 35 ኩንታል የሚጭን ተሽከርካሪ ምርመራ ሲካሄድ የሚከፈል፤
6) ከ36 እስከ 70 ኩንታል የሚጭን ተሽከርካሪ ምርመራ ሲካሄድ የሚከፈል፤
7) ከ71 እስከ 150 ኩንታል የሚጭን ተሽከርካሪ ምርመራ ሲካሄድ የሚከፈል፤
8) ከ150 ኩንታል በላይ የሚጭን ተሽከርካሪ ምርመራ ሲካሄድ የሚከፈል፤
9) እስከ 18000 ሊትር ፈሳሽ የሚጭን ተሽከርካሪ ምርመራ ሲካሄድ የሚከፈል፤
10) ከ18000 ሊትር በላይ ፈሳሽ የሚጭን ተሽከርካሪ ምርመራ ሲካሄድ የሚከፈል፤

11) የህዝብ፣ የጭነት እና የፈሳሽ ተሽከርካሪዎች በተደረገላቸው ድገተኛ የቴክኒክ ምርመራ የተገኘባቸውን ጉድለቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ አስተካክለው ካልቀረቡ የቅጣት ክፍያ።

4/ ከትራንስፖርት አገልግሎት ስምሪት፦

1) የኦፐሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት የአገልግሎት ክፍያ፤
2) የኦፐሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ለማደስ የአገልግሎት ክፍያ፤
3) የኦፐሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ እድሳት ሲያልፍበት የቅጣት ክፍያ፤
4) ለአዲስ የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት ፈቃድ ለመስጠት የአገልግሎት ክፍያ፤
5) የነባር የህዝብ የትራንስፖርት ማህበራት ፈቃድ ለማደስ የአገልግሎት ክፍያ፤
6) የህዝብ የትራንስፖርት ማህበራት ፈቃድ በወቅቱካልታደሰ ከቅጣት ክፍያ፤
7) ለአዲስ የከተማ ትራንስፖርት ማህበራት ፈቃድ ሲሰጥ ከሚከፈል፤
8) የነባር የከተማ የትራንስፖርት ማህበራት ፈቃድ ሲታደስ ከሚከፈል፤
9) የከተማ የትራንስፖርት ማህበራት ፈቃዱ በወቅቱ ካልታደሰ ከቅጣት ክፍያ፤
10) ለአዲስ የጭነት ትራንስፖርት ማህበራት ፈቃድ ሲሰጥ ከሚከፈል፤
11) የነባር የጭነት የትራንስፖርት ማህበራት ፈቃዱ ሲታደስ ከሚከፈል፤
12) የጭነት የትራንስፖርት ማህበራት ፈቃዱ በወቅቱ ካልታደሰ ከቅጣት ክፍያ፤
13) ለአዲስ የትራንስፖርት ድርጅቶች ፈቃድ ሲሰጥ ከሚከፈል፤
14) የነባር የትራንስፖርት ድርጅቶች ፈቃድ ሲታደስ ከሚከፈል፤
15) የትራንስፖርት ድርጅቶች ፈቃዱ በወቅቱ ሳይታደስ ሲቀር ከቅጣት ክፍያ፤
16) አዲስ ህዝብ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች የማህበር አባል እንዲሆኑ ፈቃድ ሲሰጥ ከሚከፈል፤
17) አዲስ የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች የማህበር አባል እንዲሆኑ ፈቃድ ሲሰጥ ከሚከፈል፤
18) አዲስ የጀልባ ባለንብረቶች የማህበር አባል እንዲሆኑ ፈቃድ ሲሰጥ ከሚከፈል፤
19) የስምሪት መልቀቂያ ሲሰጥ ከሚከፈል፤
20) የልዩ ጉዞ ፈቃድ ሲሰጥ ከሚከፈል።

5/ ከመንገድ ትራፊክ ደህንነት፦

1) ከትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች የቅጣት ክፍያ፤
2) ከመንገድ ፈንድ ከሚሰበሰብ ክፍያ።

# ንዑስ ክፍል ሁለት

# ከውስጥ ገቢ የሚሰበሰብ ገንዘብ ስራ ላይ የሚውልባቸው ዝርዝሮች

## 5. ከውስጥ ገቢ የሚሰበሰብ ገንዘብ ስራ ላይ የሚውልባቸው ዝርዝሮች

1/ የመሰረተ ልማት ግንባታ እና ጥገና ስራዎች፦

1) ለትራፊክ ኮምፐሌክስ ግንባታ እና ጥገና፤
2) ለትራፊክ ኮምፐሌክስ ግንባታ ለማማከር፣ ለቁጥጥር እና ክትትል አገልግሎት ክፍያ፣ ለግንባታና ጥገና የሚያስፈልጉ ግብዓቶች እና ቁሳቁሶች መግዣ፤
3) የትራፊክ ኮምፐሌክስ አጥር ግንባታ እና ጥገና፤
4) የአስተዳደር ህንፃ ግንባታን ሳይጨምር የአሽከርካሪ እና ተሽከርካሪ አገልግሎት በሚሰጥባቸው የቢሮ ግንባታ እና ጥገና፤
5) የአሽከርካሪ እና ተሽከርካሪ አገልግሎት በሚሰጥባቸው መዝገብ ቤት ግንባታ እና ጥገና፤
6) የአሽከርካሪ እና ተሽከርካሪ አገልግሎት በሚሰጥባቸውም ሆነ አገልግሎቱ በአዲስ በሚከፈትባቸው የሲስተም ዝርጋታ እና ጥገና፤
7) በትራፊክ ኮምፐሌክስ የሲ.ሲ.ቲ.ቪ. ካሜራ ተከላ እና ጥገና፤
8) የተግባር እና የንድፈ ሃሳብ ስልጠና እና ፈተና መከታተያ የካሜራ ግዥ፣ ተከላ፣ ጥገና፤
9) ትራፊክ ኮምሌክስ ለመገንባት የዲዛይን ማሰሪያ፤
10) ለጭነት ተርሚና ዲዛይን ማስሪያ፣ ለግንባታ እና ጥገና ስራ፤
11) ከተሞች ላይ ለመኪና ማቆሚያ (ለፓርኪንግ) ግንባታ፤
12) የተግባር እና የንድፈ ሃሳብ ስልጠና እና ፈተና ከካሜራ ጋር በሊንክ አስተሳስሮ የክትትል እና ቁጥጥር ስራውን ከሰው ንክኪ ነፃ ለማድረግ ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች ስማርት ሞባይል መግዣ እና የተገደበ ወርሃዊ የአየር ሰዓት ክፍያ፤
13) ለአሽከርካሪ እና ተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ለሲስተም ሶፈትዌር ማበልፀጊያ፣ ማሳደጊያ፣ አፕዴትማድረጊያ ስራዎች፣ የለማ ሶፍትዌር ማስጫኛ፣ ማስጠገኛ ክፍያዎች፤

14) የአሽከርካሪ እና የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ፋሲሊቲዎች ማሟያ /ለመፀዳጃ ቤት ግንባታ፣ ለኢንተርኔት ማስገቢያ፣ የኢንተርኔት አገልግሎት ክፍያ፣ ለካፍቴሪያ ቁሳቁስ ማሟያ፣ ለደንበኞች ማረፊያ ሸድ ግንባታ እና መቀመጫ ወንበር መግዣ፤

15) የአሽከርካሪ እና የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ የማስፋፊያ (መዝገብ ቤት፣ መፈተኛ ክፍል) እና የማዘመኛ ስራዎች ክፍያ፤

16) እንደ አስፈላጊነቱ ለመኖሪያ ግንባታ እና ለቴክኖሎጅ ልማት ማሰሪያ ክፍያ።

2/ ለግብዓቶች እና ለቁሳቁሶች ማሟያ፡-

1) የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች (ሰርቨር፣ የመንጃ ፈቃድ የማተሚያ ማሽን (ፋርጎ ፐሪንተር)፣ ፐሪንተር፣ ዴስክቶፕ እና ላፕቶፕ ኮምፒውተር፣ ፎቶኮፒ ማሽን፣ ስካነር፣ መቅረፀ ድምጽ፣ ፍላሽ፣ ሜጋፎን፣ ቴሌቪዥን ወዘተ…፣

2) ለሁሉም የኤልክትሮኒክስ እቃዎች ማስጠገኛ፣

3) የኮምፒውተር የማፅጃ (cleaning kit) መግዣ፣

4) የኤሌክትሪክ መብራት ሲጠፋ አገልግሎቱ እንዳይቋረጥ ጀነሬተር መግዣና ማስጠገኛ፣ ለጀነሬተር ነዳጅ፣ የመብራት ማቆያ ዩፒኤስ (ፓዎር ሴቨር ወይም ፓዎር ባንክ) መግዣ፣ ሲስኮሲዊች፣ የአሽከርካሪናተሽከርካሪ አገልግሎት በሚሰጥባቸው የኤሌክተሪክ ማስገቢያ፣ ሃይል ሲያንስ እራሱን የቻለ ትራንስፎርመር ማስገቢያ፣ ትራንስፎርመር ሲበላሽ ማስቀየሪያ፣ የኤሌክትርክ መስመር ሲቃጠል ገመድ መግዣ።

3/ ለህትመት አገልግሎት፡-

1) ለተሽከርካሪ ሰሌዳ መግዣ፣ የሪቫን፣ የኦቨር ላሚኔሽን፣ የመንጃ ፈቃድ ካርድ እና ደብተር መግዣ፣

2) ለገቢ መሰብሰቢያ ካርኒ እና የኮምፒውተር ደረሰኝ ማሳተሚያ፣ ለባነር፣ ለባጅ፣ ለተለያዩ የተሽከርካሪ ምርመራ ቸክሊስት ማሳተሚያ፣

3) ለማስታወቂያ፣ ለበራሪ ጽሁፎች፣ ፓፐሌቶች፣ የማስታወቂያ ሰሌዳ ማሰሪያ።

4/ ለቢሮ ቋሚ እቃዎች፡-

1) ለባለጉዳይ መቀመጫ ወንበር ወይም አግዳሚ ወንበር ከእንጨት ወይም ከብረት ወይም ከእንጨት ወይም ከእንጨት እና ብረት የተሰራ)፣

2) ለዶክመንት ማስቀመጫ ሸልፍ (ከብረት ወይም ከእንጨት ወይም ከእንጨትና ከብረት የተሰራ) ወዘተ...ማሰሪያ፣ መግዣ፣ ማስጠገኛ፣

3) ለአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ስልጣኞች መፈተኛ ወንበር. እና ጠረጴዛ መገዣ፣ ማሰሪያ፣ ማስጠገኛ፣

4) የስቴፕለር መምቻ (ትልቁ፣ መካከለኛ፣ ትንሽ) መግዣ፣

5/ ለቢሮ አላቂ እቃዎች፦

ለአሽከርካሪና ተሽከርካሪ አገልግሎት ለመስጠት የሚያገለግሉ አላቂ የቢሮ እቃዎች እና የፅህፈት መሳሪያዎች።

6/ የትራፊክ አደጋን ለመከላከል ለሚያግዙ ግብአቶች፡-

1) የተሽከርካሪዎችን ፍጥነት ለመቆጣጠር የራዳር መግዣ እና ማስጠገኛ፣
2) አልኮልጠጥተዉ የሚነዱ አሽከርካሪዎችን ለመመርመር ለአልኮል ቴስትር መግዣ፣
3) የትራፊክ መብራት መግዣ፣
4) የትራፊክ አደጋ መከታተያ ሲሲቲቪ ካሜራ መግዣ እና ማስጠገኛ፣
5) የትራንስፖርት ህግን ለሚያስከብሩእና አገልግሎት ለሚሰጡ አንፀባራቂ አልባሳት መግዣ፣
6) ቻርጅ የሚደረግ እና ልዩ ልዩ መብራቶች ያሉት የተቆጣጣሪ ዱላ መግዣ፣
7) የከተማ መንገዶች ላይ የዜብራ ቀለም ማስቀቢያ፣
8) የትራፊክ ምልክትና ማመለከቻ ማሰሪያ ማስጠገኛ፣
9) ስሪዲ ማፕ መግዣና ማስጠገኛ፣
10) ስቶፐር እና የክስ ፓድ ማሳተሚያ፣
11) ለመንገድ ላይ ተቆጣጣሪዎች የደረት ካሜራ መግዣ።

7/ ለአቅም ግንባታ ስራዎች፦

1) ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ የሚፈጅ የአቅም ግንባታ ስልጠና ወጭ፤
2) የስራ ባህሪያቸው አስገዳጅ ለሆነባቸው ሰራተኞች ብቻ በልዩ ሁኔታ የሚተገበር፤
3) በባለስልጣኑ እና በጽ/ቤቶች መደበኛ ስራቸው መንጃ ፈቃድ አስገዳጅ ለሆነባቸው በዓመት ከ10 ላልበለጠ ሰው የመንጃ ፈቃድ ስልጠና ክፍያ።

8/ የጀልባ ብቃት ለማረጋገጥ

አስፈላጊ ግብዓትና ቁሳቁስ ማሟያ።

9/ ለተሽከርካሪ ግዥ እና ለነዳጅ፡-

ጥያቄው በልዩ ሁኔታ ለገንዘብ ቢሮ ቀርቦ ሲታመንበት ለሰራተኞች የሰርቪስ አገልገሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች መግዣ፣ ማስጠገኛ፣ የነዳጅ፣ ለመለዋወጫና ለጎማ፣ መግዥ፣ ለኢንሹራንስ ክፍያ፣ ስራዉን በቅርበት ለመከታተል የሞተርና የመስክ መኪኖች ግዥ።

## ንዑስ ክፍል ሦሥት

## የተሰበሰበ የውስጥ ገቢ አፈቃቀድ እና አጠቃቀም

### 6. ከውስጥ ገቢ የተሰበሰበ ገንዘብ አፈቃቀድ እና አጠቃቀም፦

1/ ባለስልጣኑ የዞን ትራንስፖርት ጽ/ቤት፣ የሪጅኦፖሊታንት ከተማ ትራንስፖርት ጽህፈት ቤቶች/ቤቶችን እና የብሔረሰብ ዞን ትራንስፖርት ጽህፈት ቤቶችን በጀት ያፀድቃል፤

2/ የውስጥ ገቢ በጀትን መጠቀም የሚቻለው የዞን፣ የብሄረሰብ ዞን እና የሪጅኦ ፖሊታን ከተማ ትራስፖርት ጽህፈት ቤቶች የበጀት ጥያቄውን ለትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን አቅርበው ሲፈቀድ ብቻ ነው፤

3/ ባለስልጣኑ የበጀት ጥያቄዉን ሲፈቅድ በጀቱ እንዲለቀቅ በተዋረድ ለሚገኘዉ ለገንዘብ መምሪያዎች ማሳወቅ ይኖርበታል፤

4/ የበጀት ጥያቄ የሚያቀርቡ በክልል ደረጃ የሚመለከታቸው ዳይሬክቶሬት እና በዞን ትራንስፖርት ጽ/ቤቶች ስር ያሉ የሚመለከታቸው ቡድኖች ለበጀት አመቱ የሚያስፈልገውን በጀት እና የሚሰራዉን ስራ በዝርዝር አቅደው እቅዱን የበጀት አመቱ በገባ እጅግ ቢዘገይ በመጀመሪያው ሳምንት በክልል ደረጃ ከሆነ በዳይሬክተሩ እንዲሁም በዞን ደረጃ ጽህፈት ቤት ኃላፊዎች ተፈርሞ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፤

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተገለጸው ቢኖርም እንደስራው አስፈላጊነት እና አስቸኳይነት ታይቶ ከታመነበት ባለስልጣኑ ወይም ጽህፈት ቤቶች በማንኛውም ጊዜ እቅድ አዘጋጅቶ ማቅረብ ይችላል፤

6/ የበጀት ጥያቄው የአገልግሎት ግዥ ወይም ግንባታ ከሆነ የሚመለከተው መስሪያ ቤት

ወይም አካል የሚያዘጋጀዉ የስራ ዝርዝር እና ለስራዎቹ የሚያስቀምጠውን ገንዘብ መነሻ በማድረግ የበጀት ጥያቄ ማቅረብ ይገባል፤

7/ ከውስጥ ገቢ የሚመደብ በጀት አጠቃቀም የፋይናንስ ደንብ እና ይህንን መመሪያ የተከተለ መሆን ይገባዋል፤

8/ ባለስልጣኑ የበጀት ጥያቄ እንደደረሰው እጅግ ቢዘገይ በሁለት ሳምንት ዉስጥ በጀቱን አጽድቆ መላክ ይኖርበታል፤

9/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ የተገለጸዉ ቢኖርም የተጠቀሰው በጀት ተጨማሪ ማብራሪያ ካስፈለገው እስከ 3 ሳምንት ሊዘገይ ይችላል፤

10/ የበጀት ጥያቄው የፋይናንስ አሰራሩን ተከትሎ የቀረበ መሆኑ በዞኑ እና በከተማ ትራንስፖርት ጽ/ቤቶች ማኔጅመንት ታይቶና ፀድቆ ለባለስልጣኑ ይተላለፋል፤ በክልል ደረጃ ዳይሬክቶሬቶች እንደ ስራ ባህሪያቸው ከመረመሩት በኋላ በማኔጅመንት ተገምግሞ በዋና ዳይሬክተር ወይም በምክትል ዋና ዳሬክተር ይፀድቃል፤

11/ ባለስልጣኑ በማዕከል የተሰበሰበውን ገቢ በክልል ደረጃ የጥቅል ግዥ እቅድ እና እንደስራው ስፋት እና የገቢ አሰባሰብ መጠን ጽ/ቤቶች በጀት ደልድሎ በገንዘብ ቢሮ በኩል በክልሉ ምክር ቤት በማፀደቅ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

12/ የዋና ዋና ግብዓቶች እና የአገልግሎት ግዥ (ኢንተርናሽናል እና ጥቅል ግዥዎችን) እንዲሁም የመሰረተ ልማት ግንባታ እና ጥገና ስራዎች በክልል ደረጃ ሆኖ የዞን፣ የብሄረሰብ ዞን፣ የሪጅኦ ፖሊታን ከተሞች ትራንስፖርት ተጠሪ ጽህፈት ቤቶች የሚመደብላቸውን በጀት በክልል የማይሸፈኑ የግብዓትና የአገልግሎት ግዥ እንዲሁም የግንባታ እና የጥገና ስራዎችን በውስጥ ገቢ አሰባሰብ እና አጠቃቀም መመሪያው እና በግዥ እቅድ መሰረት ስራ ላይ ማዋል አለባቸው፤

13/ በባለስልጣኑ የሚከናወኑ የእቃና የአገልግሎት ግዥዎች እና የመሰረተ ልማት ስራዎች በተመለከተ በስሩ ለተደራጁ ልዩ ልዩ የስራ ክፍሎች በዚህ መምሪያ መሰረት የተፈቀዱ ግብዓቶችና ቁሳቁሶች እንዲሁም የአገልግት ግዥ መፈፀም እንደተጠበቀ ሆኖ ለዞን እና

ለሪጅኦ ፖሊታን ከተማ ትራንስፖርት ጽህፈት ቤቶች የሚከተሉትን ጥቅል ግዥዎችን እና የመሰረተ ልማት ስራዎችን ያከናወናሉ፦

1) ሰርቨር፣ ፋርጎ ፕሪነተር፣ ጀነሬተር፣ ዩፒኤስ፤ ሲስኮሲዊች፣ ጀነሬተር ግዥ፣
2) ሶፍትዌር የማበልፀግ፣ የማሳደግ፣ የማስጫን እና የማስፋፋት፣
3) የህትመት ውጤቶች ግዥ (ሰሌዳ፣ ቦሎ፣ ሊብሬ፣ የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ የኮምፒውተር ደረሰኝ፣ መንጃ ፈቃድ፣ ሪቫን፣ ኦቨርላሚኔሽን፣ የክስ ፓድ፣ ስቶፐር፣ ልዩ ልዩ ቸክሊስቶች)፣
4) ትራፊክ ኮምፐሌክስ ግንባታ፣ የትራፊክ ኮምፐሌክስ አጥር ግንባታ፣ በተገነቡ ትራፊክ ኮምፐሌክስ መዘገብ ቤት እና የጥበቃ ቤት ግንባታ (ጥገናው በተጠሪ ጽህፈት ቤቶች)፣
5) ለትራፊክ ኮምፐሌክስ ግንባታ የሚያገለግሉ እቃዎች ግዥ እና ተከላ፣
6) የሲሲቲቪ ካሜራ ግዥና ተከላ (ጥገናው በተጠሪ ጽህፈት ቤቶች)፣
7) ትራፊክ ኮመፐሌክስ ዲዛይን ማሰራት፣
8) ለመንገድ ደህንነት ቁጥጥር የሚያገለግሉ እቃዎች ግዥ (ራዳር፣ አልኮል ቴስተር ትራፊክ መብራት፣ የመንገድ ተቆጣጣሪዎች ዱላ እና የደረት ካሜራ፣ ስቶፐር ህትመት፣ የክስ ፓድ ህትመት፣ ስሪዲ ማፐ ግዥ ወዘተ...)፣
9) ለሚመለከታቸው አካላት የሚያገለግል ስማርት ሞባይል እና ቋሚና ተንቀሳቃሽ ዋይፋይ ራዉተር ግዥ፣

14/ የሪጅኦ ፖሊታን ከተማ ትራንስፖርት ጽህፈት ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ የስራ ማስኬጃ በጀት ይመደብላቸዋል፡፡ የትራፊክ አደጋ ለመከላከል የሚያግዙ የመሰረተ ልማት ስራዎች እና ግብአቶች ማሟላት ቅድሚያ የሚሰጥ ሆኖ በውጥ ገቢ አሰባሰብ እና አጠቃቀም መመሪያው መሰረት የሚመደብላቸውን የስራ ማስኬጃ በጀት መጠቀም ይችላሉ፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በባለስልጣኑ ከሚከናወኑ ጥቅል የእቃ እና የአገልግሎት ግዥዎች እንዲሁም የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ፣

15/ እንደአስፈላጊነቱ ዞኖች በተመደበላቸው በጀት ጥቅል ግዥ እንዲፈፀምላቸው ውክልና ሲሰጡ ባለስልጣኑ ገዝቶ ያከፋፍላል (ኮምፒውተር፣ ላብቶፕ ወዘተ......)፣

16/ ባለስልጣኑ የአገልግሎቱት ስፋት እና የተገልጋይ ብዛት፣ የአገልግሎት ተደራሽነት፣

የመሰረተ ልማት ተደራሽነት፣ ገቢ የመሰብሰብ አቅም እንዲሁም አስፈላጊ እና ያልተሟሉ የአገልግሎት መስጫ ቋሚ እቃዎች ታሳቢ በማድረግ ለክልል፣ ለዞንና ለሪጅኦፖሊታን ከተሞች የስራ ማስኬጃ በጀት ይደለድላል።

7. **በውስጥ ገቢ የማይሸፈኑ ወጪዎች**

1/ ለማንኛውም የውጭ አገር ጉዞ እና ሥልጠና፤

2/ ከአንድ ወር ለበለጠ ጊዜ የሀገር ውስጥ ሥልጠና፤

3/ ለሶስተኛ ወገን የሚሰጥ ማንኛውም ስጦታ እና ድጎማ፤

4/ ለተሽከርካሪዎች ግዥ (የክልሉ ገንዘብ ቢሮ ሳይፈቅድ፤

5/ የስራ ላይ ዋስትና፣ ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ክፍያ፤

6/ ለውሎ አበል እና መጓጓዣ፤

7/ ለተሽከርካሪዎች እድሳት እና ጥገና (በውስጥ ገቢ ከሚገዙት ተሽከርካሪዎች ውጭ)፤

8/ ለኢንሹራንስ ክፍያ፤

9/ ለኤሌክትሪክ፣ ለውኃ፣ ለቴሌኮምኒኬሽን እና ሌሎች አገልግሎቶች ክፍያ፤ እና

10/ የዉስጥ ገቢን በመጠቀም ሊተገበር ከታሰበዉ ዓላማ ዉጭ ለሚዉል ወጭ።

8. **የተሰበሰበ የውስጥ ገቢን በባንክ ስለማስቀመጥ**

1/ የሚሰበሰበው የውስጥ ገቢ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብ ቢሮ እውቅና በትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን ስም በተከፈተ "B" አካውንት ገቢ ይሆናል፤

2/ የሚሰበሰበው የውስጥ ገቢ በተቋሙ ገንዘብ ያዥ ወይም በዕለት ገንዘብ ሰበሳቢ አማካኝነት በየለቱ በትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን ስም በተከፈተ አካውንት ገቢ መደረግ ይኖርበታል፤

3/ በወሩ መጨረሻ የገቢ እና ወጪ ሚዛን ለማስታረቅ የባንክ አካውንት ማስታረቂያ (Bank Reconcilation) መስራት እና ሂሳቡ መታረቁ መረጋገጥ አለበት።

9. **የውስጥ ገቢን ማቀድ እና ገቢን ለመጠቀም የሚያስችል ፍቃድ ስለማግኘት**

ከአገልግሎት የሚሰበሰበው እና ሥራ ላይ የሚውለው የውስጥ ገቢ በክልሉ የፋይናንስ ስርዓት እና በዚህ መመሪያ መሰረት የሚፈፀም ሆኖ በየበጀት ዓመቱ ለመሰብሰብ የሚታቀደው የውስጥ ገቢ ለክልሉ ገንዘብ ቢሮ እየቀረበ በክልሉ ምክር ቤት የሚታወጅ ይሆናል።

## 10. የውስጥ ገቢን አዛውሮ ስለመጠቀም

1/ የውስጥ ገቢን ለመጠቀም እቅድ ወጥቶለት እቅዱ በሚመለከተው አካል ስራ ላይ እንዲውል ከተፈቀደ በኃላ በተለያየ ምክንያት ዝውውር ሊያስፈልግ ይችላል። ስለሆነም ዝውወሩ መፈቀድ ይኖርበታል፤

2/ በአንድ የወጪ ምድብ ውስጥ ከአንድ የወጪ ርዕስ ወደ ሌላ የወጪ ርዕስ ለማዛወር ጽህፈት ቤት ኃላፊ ሲፈቀድ ብቻ ይሆናል። ለምሳሌ ከ6200 ምድብ ውስጥ ከ6212 ወደ 6213፤

3/ ከአንድ የወጪ ምድብ ወደ ሌላ የወጪ ምድብ ማዛወር የሚቻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ትራንስፖርት እና ሎጆስቲክስ ባለስልጣን ሲፈቀድ ብቻ ነው። ለምሳሌ ከ6212 ወደ 6314።

## 11. ኦዲት ስለማድረግ

1/ በዚህ መመሪያ ተሰብስቦ ስራ ላይ እንዲውል የተፈቀደ የውስጥ ገቢ እና ወጪ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን እና በአግባቡ መፈፀሙን ለማረጋገጥ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርት እና ሎጆስቲክስ ባለስልጣን በሚቀጥረው ወይም በሚመድበው የውስጥ ኦዲተር አማካኝነት መመርመር ይኖርበታል፤

2/ በተመሳሳይ ሁኔታ የውስጥ ገቢ እና ወጪ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን እና በአግባቡ መፈፀሙን ለማረጋገጥ የክልሉ ገንዘብ ቢሮ በሚመድበው የውስጥ ኦዲተር አማካኝነት መመርመር ይኖርበታል፤

3/ ማንኛውም የፋይናስ እንቅስቃሴ በክልሉ ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ሌላ የውጭ ኦዲተር ኦዲት ይደረጋል፤

4/ የኦዲት ሪፖርት ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርት እና ሎጆስቲክስ ባለስልን እና ለገንዘብ ቢሮ መድረስ አለበት።

# ክፍል ሦሥት

# የአስፈፃሚ አካላት ተግባር እና ሃላፊነት

## 12. የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን ተግባር እና ኃላፊነቶች

1/ መመሪያው በትክክል ስራ ላይ መዋሉን መከታተል እና መቆጣጠር፤

2/ በዞኑ ትራንስፖርት ጽ/ቤቶች እና በከተማ ትራንስፖርት ጽ/ቤቶች የቀረበዉን የበጀት ጥያቄ መርምሮ ማጽደቅ እና አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

3/ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ የአገልግሎት ክፍያዎችን አጥንቶ ሊያሻሽል ይችላል፤

4/ በክልሉ ውስጥ አዲስ የአሽከርካሪ እና የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት መስጠት ለሚጀምሩ ዞኖች ተገቢዉን እገዛ ያደርጋል፤

5/ የተፈቀደው በጀት በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወስድ ያደርጋል፤

6/ የገቢ አሰባሰብ እና ወጭ አፈጻጸም በእቅድ ላይ ተመስርቶ ለታለመለት አላማ መዋሉን እና በክልሉ የፋይናስ ስርዓት እና በዚህ መመሪያ መሰረት ተቋሙ ለቆመለት አላማ ማስፈፀሚያ እንዲውል የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

## 13. የዞን እና የከተማ ትራንስፖርት ተጠሪ ጽ/ቤቶች ተግባርና ሃላፊነቶች

1/ የወጣዉን መመሪያ በአግባቡ ስራ ላይ ማዋል፤

2/ ከአሽከርካሪ እና ተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ቡድኖች የበጀት ጥያቄ ሲቀርብ በማኔጅመንት አይቶ ለባለስልጣኑ መላክ፤

3/ የአሽከርካሪእናየተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት እንዲጀምሩ የሚፈቀድላቸው ዞኖች ስራዎች በተያዘላቸዉ ጊዜ እንዲጠናቀቁ በማድረግ ፈጥኖ ወደ ስራ መግባት፤

4/ የተፈቀደውን በጀት በአግባቡ ስራ ላይ ማዋል፤

5/ የበጀት አፈፃፀሙን በየወሩ ለባለስልጣኑ ሪፖርት ማድረግ፤

6/ የገቢ አሰባሰብ እና ወጭ አፈጻጸም በእቅድ እንዲመራ በክልሉ የፋይናስ ስርዓት እና በዚህ መመሪያ መሰረት ተቋሙ ለቆመለት አላማ ማስፈፀሚያ እንዲውል የዕለት ተዕለት

ክትትል የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

## 14. የስራ ቡድኖች

1/ የውስጥ ገቢ አሰባሰብ እና ወጭ አፈጻጸም በእቅድ ላይ ተመስርቶ በዚህ መመሪያ የውስጥ ገቢ አሰባሰብ ዓላማዎችን በሚያሳካ መልኩ በክልሉ የፋይናስ ስርዓት እና በዚህ መመሪያ መሰረት እንዲፈፀም አመራር የመስጠት እና የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፤

2/ ተጨማሪ የገቢ ምንጮች የሚሰጡ አገልግሎቶችና ሌሎች አማራጮችን አጥንቶ ማቅረብ እና ዉጤት ሲገኝ መተግበር።

## 15. የግዥ እና ፋይናንስ አስተዳዳር

በሚመለከተው የስራ ክፍል በሚደረሰው የወጭ እቅድ መሰረት በክልሉ የፋይናስ ስርአት እና በዚህ መመሪያ መሰረት ስለመሆኑ አረጋግጦ ክፍያ ይፈጽማል።

## 16. በየደረጃዉ የሚገኙ የገንዘብ መምሪያ እና ጽህፈት ቤቶች

1/ ገንዘብ ቢሮ

1) በትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን ተዘጋጅቶ የሚቀርበዉን የገቢ እና የወጭ እቅድ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ማፀደቅ፣
2) ለክልል ምክር ቤት ቀርቦ የፀደቀውን የገቢ እና የወጭ እቅድ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ፣
3) ለሚሰበሰበዉ የዉስጥ ገቢ የ"B" አካውንት እንዲከፈት ለትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን እዉቅና መስጠት፣
4) የዉስጥ ገቢ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን እና በአግባቡ መፈፀሙን ለማረጋገጥ የዉስጥ ኦዲትር መድቦ ማስመርመር፣
5) የዉስጥ ገቢ አጠቃቀም ላይ የዉስጥ እና የዉጭ ኦዲተሮች መርምረዉ አስተያየት የሰጡባቸዉን ጉዳዮች አፈፃጸሙን መከታተል፣
6) በዚህ የዉስጥ መመሪያ ያልተካተቱ እና በልዩ ሁኔታ የሚቀርቡ የግዥ ጥያቄዎችን መርምሮ ምላሽ መስጠት።

2/ የገንዘብ መምሪያዎችና ጽህፈት ቤቶች

1) የገቢ አሰባሰቡም ሆነ የወጭ ስርዓቱ በመመሪያዉ መሰረት እንዲፈፀም ማድረግ፣

2) ከሚመለከተው የስራ ክፍል በሚደረሰው የወጭ እቅድ መሰረት በክልሉ የፋይናንስ ስርአት እና በዚህ መመሪያ መሰረት ስለመሆኑ አረጋግጦ የግዥ እና ፋይናስ አስተዳዳር ክፍያ እንዲፈጽም ማድረግ፣

3) ከመንግስት ግምጃቤት በጀት ጋር ሳይቀላቀል እራሱን የቻለ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸዉ አካላት ማድረስ፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 17. የመተባበር ግዴታ

ማንኛዉም የሚመለከተው አካል ይህን መመሪያ ስራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### 18. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

### 19. መመሪያውን ስለመማሻሻል

ይህን መመሪያ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በማንኛዉም ጊዜ ሊያሻሽለዉ ይችላል፡፡

### 20. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

1/ ይህ መመሪያ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ከ21/02/2016 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ነው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው ቢኖርም ይህ መመሪያ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ የሚነሳ መብት ወይም ግዴታ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በአስተዳደር ተቋሙ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

ዘውዱ ማለደ በላይ
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር